## 2. ረጋ እና ሰከን ያለች እንድትሆን ያደርጋታል

ያልተገረዘች ልጅ ቀዥቃዣና ሥርዓት የሌላት ትሆናለች የሚባለዉ አመለካከት ከልምድ የመጣ እንጂ ከሰዉ ልጅ ባህርይ ጋር ግንኙነት የለዉም ። አንዲት ልጅ ባህሏን የጠበቀችና ረጋ ያለች ልትሆንና መልካም ጠባይ ሊኖራት የምትችለዉ ከሚሰጣት ትምህርት፣ ከአካባቢዉና ከቤተሰቧ ከምታየዉ እዉነት ተነስታ እንጂ አንድ የአካሏ ክፍል በመቆረጡ ወይም ባለመቆረጡ አይደለም።

## 3. ድንግልናን ጠብቆ ያቆያል

በተለይ 3ኛዉ ደረጃ የግርዛት አይነት የሴቷን ብልት ከትልተላ በኋላ ለሽንትና ለወር አበባ ፍሰት ትንሽ ቀዳዳ ብቻ በመተዉ የሚሰፋበት ምክንያት የሴቷን ልጅ ድንግልና እስከ ጋብቻ ድረስ ጠብቆ ለማቆየት እንደሆነ ተደርጎ ይታሰባል። ይሁን እንጂ የሚሰፋዉ የሴቷ የዉጭ የብልት አካልና ክብረንጽህና /Hymen የሚባለዉ የተለያዩ ነገሮች ናቸዉ።

## 4. ወበቷን የጠበቀች እንድትሆን ይረዳል

ሴት ካልተገረዘች ቁንጥሯ እያደገ ይሄዳል። ይህም በጣም አስቀያሚና ከሴትነት የወጣች ያደርጋታል። መገረዟ ደግሞ ይህንን ችግር ከማስቀረቱም በተጨማሪ ዉበትም ያልብሳታል ተብሎ ይታሰባል። የሴት ልጅ የወሲብ ብልት አካል የሆነዉ ክፍል ካልተቆረጠ ያድጋል ብሎ ማሰብም አፈታሪካዊ እንጂ ምንም አይነት የእዉነትነት ማረጋገጫ የለዉም። የብልቷ መተልተል ወይም መሰፋት ተገራዥዋን ለስቃይ ከመዳረግ ዉጪ የሚጨምርላት ነገር የለም።

## 5. የሴት ልጅ ግረዛት ከሃይማኖት አኳያ

የሴት ልጅ ግርዛት በባህል እና በሃይማኖት እየተመካኘ ለበርካታ ዓመታት በሃገራችን ሲተገበር ቆይቷል። ይሁን እንጂ በቅዱስ ቁርአንም ሆነ በነብዩ ሙሐመድ ሐዲስ ዉስጥ የሴት ልጅ ግርዛትን አስመልክቶ የተጻፈ ነገር ያለመኖሩን የሃይማኖት ምሁራን አረጋግጠዋል።

ግርዛት ከክርስትና ሆነ ከእስልምና ሃይማኖት መጀመር 1000 ዓመት በፊት ጀምሮ በጥንታዊ ግብጽ የተጀመረ መሆኑን የአለም ጤና ድርጅት የ1997 መረጃ ይጠቁማል። ስለዚህ ነብዩ መሃመድም ቢሆኑ ስለ ግርዛት እንዲህ አሉ ከማለት በስተቀር የጻፉትም ሆነ ያስተላለፉት ትዕዛዝ የለም።

የእስልምና ሃይማኖት መፍለቂያ በሆኑት መካከለኛዉ ምስራቅ አገሮች ሳዉዲ አረቢያ፣ ሶሪያ፣ ሊባኖስ፣ ኢራን እንዲሁም ከ260 ሚሊዮን በላይ ሙስሊም በሚኖርባት በኢንዶኔዥያ፣ በሊቢያ፣ በሞሮኮና አልጄሪያ በመሳሰሉት ሀገሮች የሴት ልጅ ግርዛት የለም። እኛም ሀገር የግንዛቤ ችግርና መራጃ ከማጣት ካልሆነ በስተቀር ሊተገበር የሚያስችለዉ ምንም አይነት ምክንያት የለም። ለመሆኑ ፈጣሪስ የማያስፈልግና ጥቅም የሌለዉ አካል ፈጥሯልና እኛ ማስተካከል አለብን ብሎ ማሰብ በአላህ ዘንድ ተጠያቂ አያደርገንም?

## የሴት ልጅ ግርዛት ከሕግና ከሰብአዊ መብት አንጻር

የሴት ልጅ ግርዛት ከጤናም ሆነ ከሰብአዊ መብት አኳያ ትክክል ያልሆነና መቅረት ያለበት መሆኑን ለበርካታ አመታት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተዉ ጥናት ያካሄዱና ጉዳቱን የተረዱ ሁሉ ሲቃወሙት ቆይተዋል። በተለይ እ.ኤ.አ. 1993 ቪየና በተካሄደዉ የአለም የሰብአዊ መብቶች ጉባዔ፤ በ1994 ካይሮ በተካሄደዉ የህዝብና ልማት አቀፍ ኮንፈረንስ፤ በ1995 ቤጂንግ በተካሄደዉ የአለም አቀፍ ሴቶች ኮንፈረንስ የሴት ልጅ ግርዛት ሰባዊ መብትን የሚጥስና መቅረት ያለበት ስለ መሆኑ ከሙሉ ስምምነት ላይ ተደርሷል። ድርጊቱም እንዲወገዝ ተደርጓል።

በሀገራችን ኢትጵያም የአለም አቀፍ ስምምነቶችን የምትቀበል ከመሆኑም በተጨማሪ በቅርቡ በወጡት የቤተሰብ ሕግ፣ የሴቶችና የሕጻናት ፖሊሲዎች በዜጎች ላይ ከራሳቸዉ ፈቃድ ዉጪ በአካላቸዉ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል።

በአጠቃላይ የሴት ልጅ ግርዛት ገና የሚሰማቸዉን የስቃይ ስሜት በጩኸትና በእንባ ከመግለጽ ዉጪ ምንም እድል በሌላቸዉ ከተወለዱ ከሳምንት እድሜያቸዉ ጀምሮ እስከ ሠርጋቸዉ ዋዜማና ከዚያም በኋላ በፈቃዳቸዉ ሳይሆን የፊጥኝ ተይዘዉና ታስረዉ በጣም ስስና ስሜት ሰጪ አካላቸዉ በተገኘዉ ስለት ባለዉ መሳሪያ መቆረጡ ለተለያዩ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዉስብስብ ችግሮች የሚያጋልጣቸዉ በመሆኑ ሊቀር ይገባዋል።

ከጉዳት ይልቅ ምንም ጥቅም እንደሌለዉ በጥናት የተረጋገጠዉን የሴት ልጅ ግርዛት ለማሰቀረት የሚቻለዉ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የጋራ ግንዛቤ በመያዝ የበኩላቸዉን አስተዋጽኦ ማድረግ ሲችሉ ብቻ ነዉ። በተለይ የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆኑትና ልጆቻቸዉንም ለተመሳሳይ ስቃይ እንዲዳረጉ ከሚገፉፉት እናቶች አያቶችና ገራዦች የግርዛትን ጎጂነት ተረድተዉ ይቅር ይብቃ ሊሉ ይገባል። የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የጎሣ መሪዎችና ወጣቶች በአጠቃላይም በህብረተሰቡ ዉስጥ ተሰሚነት ያላቸዉ ሁሉ ሕዝቡን በማስተማርና በመቀስቀስ ለሴቶች የእድሜ ልክ ስቃይ ምክንያት የሆነዉን የሴት ልጅ ግርዛት ለማስቀረት ግንባር ቀደም ተፋላሚ ሊሆኑ ይገባል።

መዲና ያጋጠማትን አይነት ጉዳትና ተመሳሳይ የሴት ልጆች የስቃይ ምንጭ የሆነዉን ይህን ጎጂ የሆነ ልማዳዊ ድርጊት ለማስቀረት የበኩሉዎን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዛሬዉኑ ይወስኑ!

በራሪ ጽሑፍ እንዲደርሳችሁ ከፈለጋችሁ እንዲሁም አስተያየትና ጥያቄ ቢኖራችሁ በሚከተለዉ አድራሻ ታገኛላችሁ።

**ፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር**
ፖ.ሣ.ቁጥር 672
ስ.ቁ 0115520990/0115522690
e- mail: pmc@ethionet.et
website: www.populationmedia.org

# “ልጄን ከሴት ልጅ ግርዛት እጠብቃለሁ!”



Save the Children

POPULATION MEDIA CENTER
Acting for Change

## የሴት ልጅ ግርዛት ነጃነት

ብዙዎች ሴት ህጻናትና ወጣቶች በወላጆቻቸዉ የተሳሳተ እምነትና ፍላጎት ምክንያት ስስ ወሲብ ብልታቸዉ በህጻንነታቸዉ እየተቆረጠ፤ ሲብስም ደግሞ እየተተለተለና እየተሰፋ ለስቃይና ለሞት ሲዳረጉ ቆይተዋል። አሁንም እንደዚሁ በግረዘት ምክንያት የሞቱት፤ ከሞት የተረፉም ቢሆኑ ለእድሜ ልክ ጭንቀትና የጤና መታወክ የተጋለጡት ቤት ይቁጠራቸዉ።

“መዲና ባሏ በሞት የተለያት ገና የ3ወር እርጉዝ እንደነበረች ነዉ። የእናትዋንና የራስዋን የዕለት ጉርስ ለማሟላት ግመሎቿን ለነጋዴዎች እያከራየች መኖር ጀመረች። አንድ ዕለት ሌላ ግዜ እንደምታረገዉ ሁሉ የግመሎቿን ኪራይ ለመቀበል ከምትኖርበት ከተማ ወደ ጅቡቲ አቅጣጫ ትሄዳለች። ሆኖም ግን በወቅቱ አልተመለሰችም። ከቀናት በኋላ የተቆራረጡ አካላቷና በደም የተበከሉ የልብሷ ቁርጥራጮች ተገኙ። በኋላ ከብዙዎች ግምት ለመረዳት እንደተቻለዉ ብልቷ የተሰፋዉ መዲና ምጧ እየበረታ ሲሄድ የተሰፋዉን አካሏን ራሷ ቀድዳ መዉለድ ባለመቻሏ በአጋጠማት ስቃይ ጽንሱን ሳትገላገል ሞታ ኖሮ ለጅቦች ራት ሆናለች“

### ይህ በግርዛት ምክንያት በአፋር ክልል የተከሰተ እዉነተኛ ታሪክ ነዉ። ለመሆኑ የሴት ልጅ ግርዛት ምንድነዉ?

## የሴት ልጅ ግርዛት

የሴት ልጅ ግርዛት በአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት እ.ኤ.አ. 1995 ትርጓሜ መሰረት ከሴት ልጅ ብልት አካል የስሜትን ምንጭ የሆነዉን ቂንጥርን ወይም የብልትን ዉስጣዊ ወይም ዉጫዊ አካል ክፍልን በሙሉ ወይም በከፊል መቁረጥ ወይም በሌላ በተመሳሳይ መንገድ ተፈጥሯዊዉን የሴት ልጅ ብልት ገጽታ ለመቀየር የሚደረግ ማንኛዉንም አይነት ድርጊት ይይዛል።

## የሴት ልጅ ግርዛት ደረጃዎች

የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ጉዳቱ መጠንና አፈጻጸሙ የተለያየ ደረጃ ያለዉ ሲሆን፤ የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት በ1995 ያወጣዉ መረጃ መሰረት በ3 ዋና ዋና ደረጃዎች ተከፍሏል።

**እነሱም፤**



**ደረጃ አንድ፡-** የሴት ልጅ ብልት አካል የሆነዉን ቂንጥርን/clitoris/ በከፊል ወይም በሙሉ መቁረጥ ሲሆን

**ደረጃ ሁለት፡-** ደግሞ ቂንጥርን በሙሉና የሴት ልጅ ብልትን የዉስጥ ከንፈር /labia Minora/ በከፊል ወይም በሙሉ መቁረጥን የያዘ ነዉ።

**ደረጃ ሶስት፡-** ቀደም ሲል በደረጃ አንድና ሁለት የተጠቀሱትን ጨምሮ ከዚህም በተጨማሪ የሴት ልጅ ብልትን ዉጫዊ /አብይ ከንፈር/ /Labia Majora/በሙሉ ወይም በከፊል በመቁረጥ ለሽንትና ለወር አበባ መዉጫ ትንሽ ቀዳዳ በመተዉ የቀረዉን ክፍል በመስፋት የሚከናወነው የግርዛት አይነት ነዉ። ይህም የግርዛት አይነት በእንግሊዘኛ ኢንፊቡሌሽንስ/Infibulations/ሲባል ከአመጣጡም ጋር በተያያዘ ፈርኦኒክ/Pharaonic/ በመባል ይታወቃል።

## የሴት ልጅ ግርዛት ስፋትና ስርጭት

ከሃገራችን እድሜያቸዉ ከ15-49 አመት ከሆኑ ሴቶች ዉስጥ 65 በመቶ የተገረዙ እንደሆኑ በ2008 ዓ.ም የተካሄደ ጥናት ያመለክታል። የሴት ልጅ ግርዛት ከሚተገበርባቸዉ ክልሎች ዉስጥ የአፋር ክልል 91 በመቶ ሲሆን በሶማሌ ክልል እንደየቦታዉ ከ82-99 በመቶ እንደሆነ የተደረገዉ ጥናት ያመለክታል።

## የሴት ልጅ ግርዛት አፈጻጸም



የሴት ልጅ ግርዛት አፈጻጸም እንደ ግርዛቱ አይነትና ደረጃ እንደተገራዥዋ እና ገራዥዋ አቅምና ልምድ የሚለያይ ሲሆን አተገባበሩም ተገራዥ በድንጋይ፣ ከእንጨት ተጠርቦ በተዘጋጀ መቀመጫ፣ በአፉ በተደገፉ ገበቴ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ነገር ላይ እንድትቀመጥ በማድረግ ነዉ። ከዚህም በኃላ ስቃይዋን በጩሀት እንኳዋን እንዳትገልጽ በአካሏ ላይ በገራዥዋ የሚደረገዉን የትልተላ እንቅስቃሴ እንዳታይ አፍዋንና አይንዋን የምትይዝ ከሁዋላ፣ እጆቿንና እግሮቿን ወደቀኝና ግራ ወጥረዉ የሚይዙ ሁለት ሴቶች ከጎንና ጎን በኩል፣ ከፊት ለፊት ገራዥ ሴት ዝቅ ብላ በመቀመጥ ይከናወናል። ሕጻናቱ ግርዛቱ በሚያስከትለዉ ህመምና ስቃይ ምክንት ራሳቸዉን መቆጣጠር እስከሚሳናቸዉ ይደክማሉ። ራስን እስከመሳትና መዛል ደረጃም ያደርሳቸዋል።

## የመግረዣ መሳሪያዎች

ገራዦች ግርዛቱን ለማከናወን ቢላዋ፣ ሴንጢ፣ መቀስ፣ ምላጭ፣ የጠርሙስ ስባሪና በአካባቢዉ የሚገኝ ስለት ያለዉ የድንጋይ ስባሪ ሳይቀር ይጠቀማሉ። ግረዛቱን ለማከናወን ምንም አይነት ማደንዘዣ የማይጠቀሙ ከመሆኑም በተጨማሪ በአንድ የመግረዣ መሳሪያ የተለያዩ ሕጻናትን የሚገረዝበትም አካባቢና አጋጣሚም አለ። ደረጃ ሶስት የተባለዉ የግርዛት አይነት ከተፈጸመ በኋላ ብልትን ለመስፋት መርፌና እሾህን እንደሚጠቀሙም ታዉቋል።

በትግራይ፣ በአማራና በአርጎባ ተጎራባች በሆኑት የአፋር አካባቢዎች ሕጻናት በተወለዱ በ8 ቀናቸዉ የሚገረዙ ሲሆን በአብዛኛዉ በክልሉ ዉስጥ ግን ከአራት አመት ጀምሮ እስከ ስምንት አመት አካባቢ ድረስ ይፈጸማል።

በዚህም ምክንያት በእድሜ እየበሰሉና በአካልም እየጠነከሩ ከመጡ በኋላ የማናቸዉንም ግርዛት ለመከላከል በሚደረግ ትግልና ንቅናቄ ለበለጠ አካላዊና ሥነ- ልቦናዊ ጉዳት ይዳረጋሉ።

## የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከትላቸዉ ጉዳቶች

የሴት ልጅ ግርዛት ከሚፈጸምበት የእድሜ ደረጃ፣ የገራዥዋ እድሜና ችሎታ እንዲሁም እንደ ግርዛቱ አይነት የሚያስከትላቸዉ ጉዳቶች በርካታና የተለያዩ ሲሆኑ ጉዳቶቹም የአጭር ግዜ ማለትም ወድያዉኑ የሚጋጥሙና የረጅም ግዜ ጉዳት የሚያስከትሉ ተብለዉ ይከፈላሉ።

## የአጭር ጊዜ ጉዳቶች

ግርዛቱ የሚፈጸመዉ ያለማደንዘዣ በመሆኑና ለስላሳዉ ብልታቸዉ ሲቆረጥ የሚፈጥረዉን የስቃይ ስሜት ለመከላከል በሚደረግ ንቅናቄ ህመም ሊባባስ ብሎም የደም በብዛት መፍሰስንና ራስን መሳት ሊከሰት ይችላል።

የመግርዣ መሳሪያዎች አይነትና ስለት፣ የገራዧዋ አቅም፣ ችሎታና የማየት ብቃት፣ የተገራዥዋ ስቃዩን ለመከላከል በምታደርገዉ መወራጨት እና በመሳሰሉት ምክንያት በርካታ ሕጻናት ለሽንት ቧንቧና በብልት አካባቢ ለሚገኙ የአካል ክፍሎች መጎዳት ይዳራጋሉ።

ግርዛቱ የሚፈጸመዉ በአካባቢዉ በሚገኝ ስለት ባለዉና ንጽህናዉ ባልተጠበቀ መሳሪያ ያለማደንዘዣ በመሆኑ ለመመረዝ/ Infection/ እና በትግል ምክንያት ለሚፈጠሩ ተያያዥነት ላላቸዉ የመገጣጠሚያ አጥንቶች መፋለስና ዉልቃት ችግሮች ይዳረጋል።

ከሁሉም በላይ በደም ንክኪ ለሚተላለፈዉ ለኤች አይ.ቪ/ኤድስ በሽታና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችም ያጋልጣል።

## የረጅም ጊዜ ጉዳቶች

በግርዛት ወቅት በብልት አካባቢ በሚፈጠር መመርቀዝና ጠባሳ የሽንት ቧንቧ መመረዝ ስለሚፈጠር የሽንት መሽናት ችግር ያሳከትላል።

መካንነት፣ የወር አበባ ፍሰት ችግርና በወሲባዊ ግንኙነት ወቅት የሚፈጠር የስቃይ ስሜት ግርዛት የሚስከትላቸዉ ዘላቂ የሴት ልጆች የስቃይ ምንጭ ናቸዉ።

በብልትና አካባቢዉ በግርዛት ምክንያት በሚፈጠር ቁስለት ምክንያት ብልት ድድርና ጠባሳ ይፈጥራል። ይህም በወሊድ ወቅት ብልት እንዳይለጠጠጥ ስለሚያረገዉ ለተራዘመ ምጥ ያጋልጣል። በዚህም ምክንያት ሕጻኑ/ዋ እና እናትየዋ ለሞት ይዳረጋሉ። ከሞት የተረፉትም እናቶች ቢሆኑ ከጽንሱ የመዉጫ አካል እስከ ሽንት ፊኛና ደንዳኔ ባለዉ አካል ላይ ጉዳት ስለሚደርስ ሽንትና ሰገራን ያለመቆጣጠር ችግር /ፊስቱላ/ ያስከትልባቸዋል።

## ለሴት ልጅ ግርዛት መቀጠል የሚሰጡ የተሳሳቱ ምክንያቶች

### 1. የሴቷን ወሲባዊ ስሜት ይቀንሳል የወንዱን ይጨምራል

በርግጥ የሴት ልጅ ግርዛት ስሜት ቀስቃሽና ስሜት ሰጪ የሆኑትን የሴቷን የብልት አካላት በመቁረጥ ወይም በመግፈፍ የሚያስወግድ በመሆኑ የሴቷን ወስባዊ ሰሜት ከመቀነስ አልፎ ዘወትር ስቃይዋን እንድታስብ ያደርጋታል።

የሴቷ መገረዝ የወንዱን ስሜት የሚጨምርበት ሁኔታ ግን የለም። ይልቁንም በግርዛቱ ምክንያት የደደረዉ የብልቷ አካባቢ ለሷም ሆነ ለወንዱ የስቃይ ምንጭ በመሆኑ ችግሩ የጋራቸዉ ይሆናል።